# ቃላቸውን ባለመጠበቃቸው ዜጎችን ለሰው አውሬዎች አሳልፈው ሰጡ – ግርማ ካሳ

July 12, 2020

ለማስታወስ ያህል እነዚህ የቀድሞ ብአዴን፣ አዴፓ የአሁን የብልጽግና ፓርቲ የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራሮች ናቸው።
በነዚህ አመራሮች አማከኝነት ፣ በነርሱ ትከሻ ላይ ነው፣ ኦህዴድ ፌዴራል መንግስቱንና የአዲስ አበባ መስተዳድረን ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠረው።




እነዚህ አመራሮች አዴፓን ሲመሰርቱ አንደኛ ሕግ መንግስት እንዲሻሻል እናደርጋለን፣ ሁለተኛ አከላለሉን እናስቀይራለን፣ ሶስተኛ በሌሎች ክልሎች የሚኖሩ አማራዎች ጉዳይ ትልቁ ቱኩረታችን ይሆናል። አራተኛ አዲስ አበባ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ናት ብለው ነበር። ከሁለት አመታት በፊት። አማራ ሁሉም ኢትዮጵያ አገሩ ነው፤ በሁሉም ቦታ በሰላም ሰርቶ በነጻነት መኖር አለበት የሚለው ደጋግመው የተናገሩት ነው። ሰሞኑን ትልቅ ሰቆቃ እያየንባቸው ካሉ አካባቢዎች መካከል አንዱ የአርሲ ዞን ነው። በአርሲ ዞን ቢያንስ 20% የሚሆነው ነዋሪ ራሱን አማራ ብሎ የሚጠራ ነው። የአማራና የኦሮሞ ድብልቁ የሆነ ግን ኦሮሞ ነኝ የሚለውን ከወሰድን ደግሞ ወደ 40% ይሆናሉ። በዚያ የሚኖሩ የሸዋ ኦሮሞዎች በዚያ ባሉ በአርሲ ኦሮሞዎች እንደ "አማራ" የሚቆጠሩ ናቸው። "አማራ" የሚባሉት የሸዋ ኦሮሞዎች ስንጨምር አብላጫ ቁጥር ነው የሚኖራቸው።

ይሄንን እንኳን ከግምት በማስገባት እነዚህ የቀድሞ አዴፓ አመራሮች በዚያ የሚኖረው የአርሲ ኦሮሞ ያልሆነው ሌላው ማህብረሰብ (ከሸዋ የመጡ ኦሮምዎችን ጨምሮ) ደህንነቱ እንዲጠበቅለት፣ መብቱ እንዲከበርለት፣ ውክልና በዞኑ እንዲያገኝ ማድረግ አልቻሉም። በመሆኑም ይሄ ማህረሰብ በአገሩ እንደ ጠላትና እንደ መጢ በጽንፈኛ እየታየ በአርሲ ጽንፈኛ ኦሮሞዎች እየታደነ ነው።

አሰላም ከተማን ውሰዱ። የአሰላ ከተማ ሕዝብ አብዛኛው አማርኛ ተናጋሪ ሆኖ፣ የከተማዋ ከንቲባ ግን ከአሰላ ውጭ የመጣች ጽንፈኛ የቀድሞ ኦህዴድ አሁን የብልጽግና አመራር ናት። የጃዋር መሐመድ ወዳጅና ደጋፊ። ብአዴን አዴፓዎች ይሄንን እንኳን እንዲሻሻል ማስደረግ አልቻሉም።

በአዲስ አበባ ከአርሲና ከባሌ የመጡ ጽንፈኞችን እነ አቶ ለማ መገርሳና፣ ኢንጂነር ታከለ ኡማ አስፍረው፣ አደራጅተው የአዲስ አበባን በአዲስ አበባና በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ ማህረሰባት ሲያሸብሩ እነዚህ አመራሮች ምንም ነገር ማድረግ አልቻሉም።

ደፍሬ ይሄን እላለሁ። እንደ አርሲ ባሉ ቦታዎች የአርሲ ኦሮሞ ባልሆኑት ላይ እየደረሰ ላለው ሰቆቃ ፣ ብአዴኖች/አዴፓዎች ሃላፊነት መውሰድ አለባቸው። ሰዉን ያስጨረሱት በተዘዋዋሪ መንገድ እነርሱ ናቸው። ምንም ነገር ባለማድረጋቸውና የኦሮሞ ጽንፈኝነት መረን ሲለቅ አደጋዉን ማየት ባለመቻላቸው፤ ወይንም ማየት ባለመፈለጋቸው።